# መስዋዕትነት - የጀግኖች የመጨረሻ ቃል

ከበልጅግ ዓሊ

-፩-

## ለሽብር (2)

እዚህ ቁጭ ብዬ ከወንበሬ ላይ ፣
ሲጃራ እየማግሁ እየጠጣሁ ሻይ ፣
መጽሐፍ እያነበብኩ ቀለማት ስጭር ፣
ወጣቶች ባስተምር ፣
እዚህ ቁጭ ብዬ ስጸጽፍ ግጥም ፣
ቅርጽ ይዞቱ ወና ፣ለወኔ አይጣፍጥ ፣ለአእምሮ አይጥም ፣
ዘመኑን አይቀረፅ ፣አዋይ አይመዘገብ ፣
አያኖር አይከትብ ፣
እዚህ ቁጭ ብዬ ፣እንዲህ ቁጭ ብዬ ፣ሁሉን ክስተት ሳይ ፣
ስንት ታሪክ ያልፋል? በገሀድ ከፊቴ ፣በሃገሬ ላይ ።

ኅዳር 1970
ፈቃደ አዘዘ

ፈቃደ አዘዘ ይህንን ግጥም በሚጽፉበት ጊዜ ምን ተመልክተው ይሆን ? ኅዳር ወር 1970 ዓ. ም ኢትዮጵያ ውስጥ ቀይ ሽብር በጣም የተጧጧፈበት ወር ነበር ። በየመንገዱ የዜጎች እሬሣ ተጥሎ የሚውልበት ፣ እናት የልጇን ሬሳ እንዳትነካ የተከለከለችበት፣ ቤተሰብ ለሚወዱት ወገናቸው በማልቀሳቸው ምክንያት የተገረፉበት ወቅት ነበር ። ያንን ዘመን ይሆን በፊታቸው በገሃድ የተመለከቱት? በቅርብ ደግሞ በገሃድ የተመለከትነው ሌላ አሰቃቂ ታሪክ አለ ። በኅዳር 1997 ዓ.ም እንደገና በሃገራችን ይህ ሰቆቃ ተደገመ ።በፋሽሽቱ መለስ አዛዥነት በአጋዚ ጦር የንፁሃን ደም ፈሰሰ።

ሃገራችን ያለችበትን አምባገነናዊ ሥርዓት ከሚያንፀባርቁት ነገሮች አንዱ  በድህረ ምርጫ 97 በወያኔ ፋሽስታዊ አገዛዝ በአደባባይ የተጨፈጨፉት ንጹህ ዜጎች ናቸው። ታሪካቸውንም የሚረሳ ይኖራል ብዬ አልገምትም ። በመላው ሃገሪቱ ውስጥ ቁጥራቸው  በውል የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን በሥውርም በግልጽም ተገድለዋል ደብዛቸውም ጠፍቷል። እነዚህን ሰማዕታት የተሰውበትን አምስተኛ ዓመት ለማስታወስ ሲባል የተዘጋጀውን ማስታወቂያ ከሰማዕታት ፎቶ ጋር በየድረ ገጹ ስንመለከተው የብዙዎቻችን ልብ በሃዘን ይሰበራል ። ገና በእድሜቸው ለጋ የሆኑ ወጣቶች ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸው ብቻ እንደ ጥፋት ታይቶ በጥይት ተቆሉ ።በግፍ መገደላቸው ሳይበቃ  አስከሬናቸውም "ሽብርተኛ " " አደገኛ ቦዘኔ " የሚል ቅጽል ስም እየተሰጠው ተንገላታ። ከዚች ዓለም ጣፋጭ ኑሮ ተለያዩ ፡ ለዛች ለሚወዷት አገራቸው ታላቁን መስዋዕትነት ከፈሉ ። መስዋዕትነት መክፈል ምን ያህል ከባድ ነው ? በቤተሰቦቻቸው ላይ የደረሰውስ ሀዘን ምን ያህል ነው ? ልጄ ደረሰልኝ ወይም ደረሰችልኝ ሲሉ በባዶ የቀሩትስ ወላጆች ? የሰማዕታት ትውስታና ታሪክ የቤተሰብ ሃዘን ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም ።

ታሪካችንን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ ከውጭ ሃገር ወራሪዎች ጋር የሃገራቸውን ድንበርና የሕዝባቸውን ነፃነት ላለማስደፈር በጀግንነት ሕይወታቸውን የሰውትን የኢትዮጵያ ቁርጥ ቀን ልጆች እንድናስታውስ ግድ ይለናል። አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በፋሽሽት ኢጣሊያ የአምስት ዓመት ወረራ ወቅት በግራዚያኒ አዛዥነት የካቲት 12 ቀን የተደረገው ጭፍጨፋ ከኢትዮጵያውያን ሕሊና የማይፋቅ ታሪክ ነው ።

በሃገር ውስጥም ቢሆን ሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥን ለማምጣትና ዲሞክራሲን በሃገራችን ለማስፈን የተደረገው መራራ ትግል አለ መስዋዕትነት አልታለፈም ። በአምባገነናዊ አገዛዝ የሕዝቡን ተስፋ የሚያጨልሙ ከፋሽሽት ኢጣሊያ ባልተናነሰ ብዙ በደል ፈጽመዋል ። በመንግስቱ ኃይለማርያም መሪነት የተጀመረው ጭፍን ጭፍጨፋ ፣ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር በሃገራችን ታሪክ ላይ  የጣለው አሳፋሪ ምግባር ለብዙ ዘመናት ቁስሉ ሊድን አልቻለም ።

ከዛም በመቀጠል በሃገሪቷ ውስጥ በወያኔ ግንባር ቀደም መሪነት በተፈጠረው የዘር መከፋፈል በየቦታው በወያኔና መሰሎቹ የተገደሉትን ንጹሕ ኢትዮጵያውያንን ሁል ጊዜም ታሪክ ያስታውሳቸዋል ። የበደኖና የአሶሳን ጭፍጨፋ የሚረሳ አይደለም ። በወያኔ ዘመን የኢትዮጵያ አንድነት ይጠበቅ  ፣ዴሞክራሲ ለሕዝብ የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ  አረመኔያዊ የሆነ ጭፍጨፋና ከፋፋይ የሆነ ቅስቀሳ ቢደረግም ሃገራችን ይህንን እኩይ ዓላማ የሚዋጉ፣ ክቡር ሕይወታችውን የሚሰውላት ልጆች አላጣችም ።

መስዋዕትነት ለአንድ ሃገር ለሁለት ቁም ነገሮች አስፈላጊ ነው ። በመጀመሪያ የሚቀጥለው ትውልድ በሠሩት ቁም ነገር ፣ ሕይወታቸውን ለሃገራቸው በመክፈላቸው ሲኮራባቸው በሌላ በኩል ደግሞ ተከታዩ ትውልድ የተሰውትን ታሪክ እየሰማ ፣ ምሳሌነታቸውን እየወሰደ እንደ እነርሱ ለመሆን ጥረት ስለሚያደርግም ነው። ስለዚህም ዜጎች በሃገራቸው ውስጥ የተነሱትን ታላላቅ ሰዎች፣ መስዋትነትን የከፈሉትን በሙሉ ታሪካቸውን ሊያውቁት ይገባል ። ሃገራቸው በምን ዓይነት ሁኔታና ታሪክ እዚህ እንደደረሰች የማያውቅ ግለሰብ ስለ ሃገሩ ያለው ግንዛቤ ያነሰ ይሆናል ። ለጥፋትም ይነሳል ። አስተሳሰቡም አድማስን አያቋርጥም ።

የሃገርን አንድነት ለማስጠበቅ መሪዎቻችንና የኃይማኖት አባቶቻችን ሳይቀሩ መስዋዕትነትን ከፍለዋል ። አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዞች እጄን አልሰጥም ብለው እራሳቸውን ነው ያጠፉት ፣አፄ ዮሐንስም ከድርቡሾች ጋር ተዋግተው ነው ያለፉት ፣አቡነ ጴጥሮስ ሰኔ 21 ቀን 1931 እንኳን እኔ  ምድሪቱም ለፋሽሽት አትገዛም ብለው በጣሊያን ባንዶች በአደባባይ በጥይት ተደብድበው ነበር የተገደሉት ። ተሰፋዬ ደበሳይ የኢሕአፓ መሪ የነበረው ለፋሽሽቶች እጁን ላለመስጠት ራሱን ነው ያጠፋው ። ተሰፋዬ ታሰደ ፣ አሰፋ ማሩ ፣ ፕሮፌሰር አስራት እነዚህ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው ። የሚያኮሩንና ምሳሌ የሚሆኑን መሪዎች ሲኖሩን የሚያዋርዱ መሪዎችም እንደነበሩን አንዘነጋውም ። በተለይ በቅርብ ዘመን ሃገራችንን የመሩት መስዋዕትነትን ይሸሹ እንደነበር የታየ ነው ። አፄ ኃይለሥላሴ በጠላት ወረራ ዘመን አርበኛውን ጥለው ሄደው በፈረንጅ ሃገር ተቀመጡ ብሉ ሲወቅስና "እኔ እንደ አፄ ቴዎድሮስ ነኝ" ብሎ ሲለፍፍ የነበረው መንግሥቱ ኃይለማርያም የቁርጡ ቀን ሲደርስ ጨርቁን ሰብስቦ ፣ ጦሩን በትኖ ወደ ሃራሬ ነው የፈረጠጠው ። አንዳንድ የቅንጅት መሪዎችም ዛሬ ቀናቸውን የምናስባቸው ወጣቶች መስዋዕትነትን በተቀበሉ አምስት ዓመት ውስጥ እጁ በደም በተጨማለቀው ከፋሽሽቱ የወያኔ መሪ ጋር ሲጨባበጡ ነው የታዩት ።ታሪክ እነዚህ ሁሉ መዝግቦ ይዞ ይገኛል ።

ስለ መስዋዕትነት ከተነሳ ዘንዳ  በሃገራችን ታሪክ ውስጥ ሳይነሳ  መታለፍ የሌለበት ታሪክ ባነሳ እወደላለሁ ። ይህም በዘመነ ዘርአ ያዕቆብ የተፈፀመ የአባ እስጢፋኖስና የተከታዮቻቸው ታሪክ ነው ። ታሪኩን በዚህ በሰማዕታት ወር ውስጥ ማንሳቱ አስፈላጊ የሚያደርገው በሁለት ቁም ነገር ምክንያት ነው ። አንደኛው ሰማዕታቱ ለተሰውለት ዓላማ በቁርጠኝነት እስከመጨረሻው ድረስ ስለታገሉ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በወቅቱ የነበረውን ታሪክ በጽሁፍ በጥሩ ሁኔታ ሰላስቀመጡት ነው ። ይህንን የኢትዮጵያ ታሪክ በውጭ ያሉ ምሁራን እንኳን ሳይቀሩ የተከታተሉት ሲሆን ከባሕላዊ ትምህርት ተገልሎ በዘመኑ ትምህርት ውስጥ የተጓዘው ኢትዮጵያዊው ትውልድ ሳያውቀው  ወይም ሳይሰማው አልፏል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው "ደቂቀ እስጢፋኖስ" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ  መጽሐፉ ለምን እንደተጻፈና ፣ ታሪኩስ እንዴት እንደነበረ መግቢያው ላይ  እንዲህ ብለው ይገልጹታል ፡ -

> ታሪካቸውን እዚህ የማቀርበው አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው (ደቂቀ እስጢፋኖስ ) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸው እንዲያውም የተወገዙ አድርጋ የምታያቸው በዓሥራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት ያበቡ የተሐድሶ መሪዎች ናቸው ። አሕይዋና ተሐድሶ ( Revival and Renewal or Reformation ) ተደላድሎና ተመቻችቶ በተቀመጠው ሥርዓት (Establishment) ውስጥ የዛገና የሚራገፍ ነገር የሚያይ የአእምሮ ችሎታና የተፈጥሮ ተሰጥዎ ካላቸው ታላላቅ ሰዎች ዘንድ የሚመጡ ሐሳቦች ናቸው።  እነዚህ ሰዎች "መለወጥ አለበት" የሚሉትን ለመለወጥ ቆርጠው ሲነሱ ደግሞ ታላቅነታቸው ወደ ገናናነት ያድጋል። ትውልድም አገሪቱ የነፃ ሐሳብና የምርምር ሰዎች እንደነበሯት ሲያውቅ ይኮራል ። የደቂቀ እስጢፋኖስን ገድሎች የማሳትመው በኛም አገር የሚያኮራ የአእምሮ እንቅስቃሴና ለእምነት መሞት የነበረ መሆኑን ላላዩ ለማሳየት ነው እንጂ እንቅስቃሴውን ለመደገፍ ወይም ለመቃወም ወይም እንደነሱ የንጉሥ ግርማ የማይፈሩ መንፈሳዊ አባቶች አልነበሩንም ለማለት አይደለም ። አባ አኖርዮስና አባ ፊሊጶስ አፄ ዓምደ ጽዮን የአባቱን ዕቅብት ቢያገባ ሳይፈሩ ተናግረውታል ። የቀጣቸውም ቅጣት ቀላል አልነበረም ። ገድላቸው እንደሚመሰክረው ደማቸው እንደውሐ እስከሚፈስ ገርፏቸዋል፣ ራቁታቸውን በገበያ መካከል አስኪዷቸዋል ፣አግአዟቸዋል ። ቅጣቱ ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ቅጣት ቢያንስ የእነሱን ቆራጥነት አያሳንሰውም ።
>
> ገጽ 23

ደቂቀ እስጢፋኖስ የተነሱት በአፄ ይሥሐቅ ዘመን (1406 – 1421 )ነው ።አባ እስጢፋኖስ ምንም እንኳ በአፄ ይሥሃቅ ችሎት ቀርበው ተመሳሳይ ሃሳብ አቅርበው የተመሰገኑ መነኩሴ ቢሆኑም በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ግን ተወግዘው ነበር ። በየትም አገር ቢሆን በተደላደለው ሥርዓት ላይ ተመቻችተው የተቀመጡ ኅላፊዎች የግል ምኞታቸውን የሚፃረር ፣

ሥልጣናቸውን የሚቀናቀን ለውጥ ስለሚጠሉ እንዲህ ያለውን ጥሪ ይቃወሙታል። ከመቃወምም አልፈው ለውጥ ፈላጊዎችን ባላቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ኀይል ሁሉ ሊያጠፏቸው ይሞክራሉ። በአባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ደቂቀ እስጢፋኖስ የደረሰው ይህ ነው ።

አምባገነናዊ አስተዳደር የሚመሩ ባለሥልጣናት ለውጥ ፋላጊዎችን ለጊዜው ማጥፋትና ሃሳባቸውን ማኮላሸት ብቻ ሳይሆን በታሪክ ተወቃሽ ላለመሆን ክፉ ሥራቸውን የሰው ክቡር ሕይወት ማጥፋታቸውን ለመካድ ጥረት ያደርጋሉ ። የመንግሥት ሥልጣን የያዙ ሰዎች ተቃዋሚዎቻቸውን ሊያጠፉ ሲፈልጉ ሁል ጊዜም ቢሆን የሚሰጡት ምክንያት አለ ። ለምሳሌ በቀይ ሽብር ዘመን ፋሽሽቱ መንግሥቱና ተከታዮቹ ይገድሉ የነበሩት " **አድሃሪ ፣ የሲ.አይ .ኤ ቅጥረኛ ፣ አናርኪስት ፣ ፀረ ሕዝብ፣ አሻጥረኛ ወዘተ ፣** " በሚል ምክንያት ቢሆንም በወቅቱ ደማቸው እንደጎርፍ ይወርድ የነበረው ግን ለውጥ ለሃገራቸው ለማምጣት ከሚታገሉ ወጣቶች እስከ የሃይማኖት ሰዎች ፣አዛውንቶች ጨምሮ መሆኑ አይዘነጋም። ይህንን ሁሉ ዓይን ያወጣ የአደባባይ ምሥጢር የሆነ ፋሽሽታዊ ሥራ የመንግሥቱ ደጋፊዎች አሁን ድረስ " *መንግሥቱ አገር ወዳድ ነው* " የሚል ቅጽል ስም በመስጠት እንደ ገደል ማሚቱ ጩኸት ሲያስተጋቡ ይታያሉ ። እውነታው ግን አምባገነኑ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዓላማው ሥልጣኑን እስከቻለው ድረስ ጠብቆ ማቆየት ብቻ ነበር ። የመስዋዕትነቱ ጊዜ ሲደርስ ለምን አልሞታችሁም ብሎ የሰዎችን ቂጥ በሳንጃ እንዳልወጋ አንድም ጥፊ ሳይቀምስ ቀድሞ አጎቱን አሥራት ወልዴን ልኮ ወደ አዘጋጀው ቤቱ ነው የሮጠው።በወያኔም ዘመን ተመሣሣይ ድርጊት እያየን ነው ። የኢትዮጵያውያን ጥያቄ የዴሞክራሲ መሆኑን የሚከድ አይኖርም ።

አፄ ዘርአ ያዕቆብም አባ እስጢፋኖስንም ሆነ ተከታዮቻቸውን ሲያሰቃይና ሲገድል ከአነሱት ጥያቄ ውጭ በሕዝብ ያስጠላቸዋል የሚለውን የሃይማኖት ጥያቄ ጨምሮ እንደወነጀላቸው ታሪክ ያስረዳል። እውነታው ግን ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፍ ውስጥ ቀርቧል ።

> አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ስግደት ከአምልኮት ጋራ ስላያያዙት ከሰው ጋር ሰላምታ ሲለዋወጡ እንኳን አንገታቸውን ሰበር አያደርጉም ። ሰነዶቻቸው እንደሚመሰክሩት ፣ስግደት ለእግዚአብሔር (ለአብ ፣ለወልድ፣ለመንፈስ ቅዱስ )ካለሆነ በቀር ለሌላ አይገባም ይላሉ ። ንጉሡን ከችሎቱ ለጉባኤ የተሰበሰበውን ሕዝብ ሁሉም ራሳቸው ዝቅ በማድረግ (ምናልባትም ከመሬት ላይ በመውደቅ ) ሰላምታ ሲሰጡት እነ አባ እስጢፋኖስ ከፊቱ እንደ ጅብራ ተገትረው ይቀራሉ ። "ለምን አታጎነብሱም "ሲላቸው ለሰው መስገድ አይገባም ፣ለሰው መስገድ አምልኮ ባዕድ (አምላክ ይልሆነን ማምለክ ) ነው ። ይገባል ካልክ ሕግ ይዳኘን ብለው ምንም ነገር ሳይፈሩ በሕግ ቀጥ አድርገው ይከራከሩታል። ጻድቆቹ ሳይቀሩ ፣ለታላቅና ለባለሥልጣን ሰላምታ ሲሰጡ እንደሚያጎነብሱ (እንደሚሰግዱ) መጽሐፍ ሲጠቀስባቸው " ለማስረጃነት ከነሱ ድክምት ይልቅ የማያልፈው የእግዚአብሔር ቃል ይበልጣል ፣ከኔ በቀር ለሌላ ለማንም አትስገዱ ብሏል " ይሉታል። በእምነታቸው ሲጸኑበት አይቀጡ ቅጣት ይቀጣቸዋል ።
>
> ገጽ 29

በዚህ አጭር ጽሁፍ ስለ ደቂቀ እስጢፋኖስ ታሪክ ጽፎ ለመጨረስ ይከብዳል ። የዚህም ፅሁፍ አላማ ደቀቂ እስጢፋኖስ ትክክል ናቸው ወይም አይደሉም ለማለት ሳይሆን በወቅቱ በእነርሱ ላይ የደረሰውን መከራና ሥቃይ ለማሳየት ነው ። በዛ ዘመን በእነዚህ ለንጉሥ ማጎንበስን በተቃወሙ ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰው ግፍ ተጽፎ አያልቅም ። ለመጥቀስ ያህል ፡ -

> ከዚያም ንጉሡ እንዲደበድቧቸው አዘዘ ። በዐውድማ እንዳለ የእህል ነዶ በዱላና በብትር ደበደቧቸው ። ከዚያም ንጉሡ " ወርቅ የወደድክ ወርቅ አጠጣሃለሁ ብሏል አሁንም አፉን አቅኑና ሰርኑን ስበሩት ፣ደሙን በአፍንጫው ይጠጣ አለ።. . . . . ወታደሮቹም እንዳዘዛቸው አደረጉ ፣ ኢጋድመውም ገረፏቸው ። ሁሉንም ኢጋድመው ጤጤ በምትባለው በመግረፊያ ጅራፍ ገረፏቸው።ከዚያ ቁጣውን ከስተነፈሰ በኋላ ወዲያ ውሰዷቸው አለ።
>
> በማግስቱ እንዲያመጧቸው አዘዘ ፣እንደታሰሩም አመጧቸው ። ከሰቀላው ሰፈር አውለው ሲመሽ ከፊቱ እንዲያቆሟቸው አዘዘ። (ሲቆሙ) ለንጉሡ ስገዱ አሏቸው ። ቅዱሳኑ አንሰግድም አሉ ። "ጣላቸው ፣የትላትናው አልበቃህም" ብሎ እንዲገርፏቸው አዘዘ ። ያንን ወንድም (ጳውሎስን)አእምሮውን እስኪያጣ ድረስ ብዙ(ገረፉት) ። ያቺም ከዋሻው ወጥታ

ከነሱ ጋር የሆነችው መነኩሲት በግርፊያው ተለክፋ (ሰማዕተትነቷን ) እስክትፈጽም ድረስ ብዙ ተገረፈች።

ገጽ 137

በንጉሡ እንደታዘዙት አደረጉባቸው ፣ከቅዱሳኑ ውስጥ ቁጥራቸው 20 የሆነ ታላላቆቻቸውንና ሽማግሌዎቻቸውን ወስደው ምላሳቸውን ቆረጡት ፣ ቋንጃቸውን መዘዙት ።የቀሩት ወንድሞችና ምእምናት በደረሱበት ሁሉ እንዲታወቁ የቀኝና የግራ ጉንጫቸውን በ"ዘ" ፊደል (ቅርጽ) በረጅሙ ተለተሉት ። ("ዘ" የዘርአ ያዕቆብ ኅጻር ነው ፣መልዕክቱም የዘርአ ያዕቆብ ባሪያ ማለት ነው ።)

ገጽ 158

ከእነዚህ የአባ እስጢፋኖስ ተከታዮች ሁለት ነገር ልንማር እንችላለን ። አንደኛው ለአመኑበት እምነት በቆራጥነት ያ ሁሉ መከራ ቢደርስባቸውም እንኳ ሥልጣን ላይ ካለው ንጉሥ በመከራከር ፣ እምነት ብለው የያዙትን በማስረዳት መስዋዕትነትን ከፍለዋል።በሁለተኛ ታሪካቸውን ወዲያውኑ በጽሁፍ በማስፈር ለሚቀጥለው ትውልድ ጥለው አልፈዋል ።
አሁን በሥልጣን ላይ ቁጢጥ ብሎ የተቀመጠው ወያኔም ሥልጣኑን የሚያደላድለው እንደ ድኀረ ምርጫው የኅዳሩ ጭፍጨፋ በግልጽና በአደባባይ በስውር ደግሞ በሃገራችን የቁርጥ ቀን ልጆች ደምና አጥንት ላይ ነው ። እነ ገብረ እግዚአብሔር (ጋይም) ፣ ተስፋዬ ታደሰ ፣ አሰፋ ማኅ እንዲሁም ሌሎቹ ልንረሳቸው የማይገባን ሰማዕቶቻችን ናቸው ።

የተነገረ ይረሣል ፣ የተፃፈ ይወረሳል እንደሚባለው ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ መስዋዕትነት ለሃገራቸው ሲሉ የከፈሉ ዜጎች ስማቸው ታሪካቸው ቀስ በቀስ ሊረሳ ይቻላል። ድርጊቱ ከተፈጸመ ቆይተው የሚጻፉት ታሪኮች እውነቱ እየተረሳ በመሰለኝ ስለሚጻፉ ደግሞ ተአማኒነታቸው በጣም ያነሰ ፣ እውነትነታቸው የሚያጠራጥር ይሆናሉ ። በአንዳንድ ቦታ በቀይ ሽብር የተገደሉ ሰማዕታት በሚጠቀሱበት ጊዜ ሙሉ ስም የማይገኝበት ግዜ አለ ። ፎቶግራፎች አይገኙም ። በዚህም ምክንያት ታሪካቸውም ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ አዳጋች ይሆናል። አሁንም ይኸው ስህተት ሳይታረም በወያኔ የተጨፈጨፉትን ወጣቶች ስምና ታሪክ በውል ማወቅ አዳጋች ሆኗል። በየጊዜው በወያኔ ፋሽሽታዊ አገዛዝ ሰለባ የሚሆኑ ዜጎች ስምና ታሪክ ተመዝግቦ ለሚቀጥለው ትውልድ ሊተላለፍ ያስፈልጋል ። ያ ካልሆነ ግን ሰማእታቱም በታሪክ ሊታወሱ አይችሉም ። እየዋለ እያደርም ተግባራቸው ትውልድን አያኮራም ።

ታሪክን በጽሁፍ መስቀመጥን በሚመለከት ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፍ ላይ ቀዳሚ ቃል የሰጡት ተባባሪ ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ እንዲህ አስቀምጠውታል ።

> ይህ እንቅስቃሴ ( ማለትም የእነ አባ እስጢፋኖስ ) ከሚታወቅበት ነገር አንዱ ታሪኩን በጥሩ ሁኔታ ጽፎ ማለፉ ነው ። እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቃለው የቀረቡት አራት ምንጮች ዋናዎቹ ሥራዎች ቢሆኑም ሌሎች አያሌ ገድሎች እንዳሉ ይታወቃል ። እነዚህ ገድሎች የተጻፉት ቅዱሱ (አባ እስጢፋኖስ) ከሞተ ካጭር ጊዜ በኋላ ስለሆነና ታሪካዎቹም ባብዛኛው ያተኮሩት ሐቁን ሪፖርት ማድረግ ላይ ስለሆነ ተአማኒነታቸው በምሁራን ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቷል ።

ገጽ 16-1

የሰማዕታትን ታሪክ በምናስብበት በዚህ ወር ጥያቄያችን ንጽሐን ዜጎች አላግባብ መታሠርና መገደል ይቁም ነው።የተገደሉትም ስለ ሃገራቸው ክብር የወደቁ በመባል ታሪክ ሰማዕታትን በክብር ቦታ እንዲያስቀምጣቸው ነው ። ትላንት በደርግ በቀይሽብር የተጨፈጨፉትን በሞላ ልናስታውሳቸው ይገባል ። ከዚህም በኋላ በወያኔ በመለስ ትዕዛዝ በ97 ምርጫ መስዋዕትነት የተቀበሉትን ልንረሳዋቸው አይገባም ።የኔ ፓርቲ አባል ነው ፣ እኔን የምደግፈው ነው ሳንል ለሃገራችን አንድነትና ዴሞክራሲ ሲሉ የተሰውትን ሁሉ እንደ ሃገሪቱ ብርቅዬ ዜጋዎች ታሪካቸውን ልንጽፍ ፣ መረጃዎች ሳይረሱ ልንሰበስብ ያስፈልጋል ። የሰማዕታት ታሪክ ጥቂት በሆኑ ታዋቂ ግለሰቦች ላይ ብቻ ሊያተኩር አይገባም ።

በተለይም ደግሞ አባሎቻቸው ሕይወታቸውን የገበሩበትን ድርጅትና ዓላማ ለግል ሥልጣን ጥም ማርኪያ ሲባል ዓላማውን መተው ፣ ድርጅቱን ማፍረስ፣ በእንቶ ፈንቶ መከፋፈል ምን ያህል በታሪክ ዘንድ ተወቃሽ እንደሚያደርግ ልንጠራጠር አይገባም ። ፕሮፌሰር አሥራት ተሰውተዋል ግን የቆሙለት ዓላማ አልተፈፀመም ። ገብረ እግዚአብሔር

(ጋይም )ተሰውቷል ፣ ዓላማው ወያኔን ጥሎ ዘረኝነትን ማጥፋት ነው ። ጓዶቹ ትግሉን ሊቀጥሉ ይገባል ። ብዙ ስማቸውን የማናውቃቸው ዜጎች በድብቅ በወያኔ ይገደላሉ ። ትግሉ መቀጠል አለበት ። አዲሱ ትውልድ አቋማቸው ወይም ዓላማቸውን ከግል ጥቅማቸው አንፃር በማየት እንደ እስስት የሚለዋወጡትን ፖለቲከኞችን እንደ ምሳሌ ሊቀበላቸው አይገባም ። እንደ አባ እስጢፋኖስና ደቂቀ እስጢፋኖስ ራሳቸውን ለቆሙለት ዓላማ የሚሰውትን እንጂ ።

## ከራስ ጋር ምልልስ

ሁለት ሞት ከመሞት ፣ከብርንም ተገፍፎ፣
ቢሞቱም ግድየለ ፣ ከእምነት ጋር ተቃቅፎ፣
ጎሊናን ገስጾ፣
አንጀትንም ገርፎ።
ቢሞቱም ግድ የለ ።

ፈቃደ አዘዘ
(ከራስ ጋር ምልልስ ፣ 1967)

beljig.ali@gmail.com

መስዋትነት ስለከፈሉ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይከረም ።

ሎንዶን ጥቅምት 2010